አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like The River

# ለአዋሽ ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች
# የጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ

የአዋሽ ባንክ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 28ኛ እና 29ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔዎች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣ 367(1)፣ 370፣ እና 393፣ እንዲሁም በተሻሻለው የባንኩ የመመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 18 እና 24 መሠረት ቅዳሜ ህዳር 14 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በቅደም ተከተል በአዲስ አበባ ስካይላይት ሆቴልይካሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የተከበራችሁ የባንኩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባዔዎቹ ላይ እንድትገኙልን የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን በአክብሮት ያስተላልፋል፡፡

## 1. አክሲዮን ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

1.1. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ፣ ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 07፣ የቤት ቁጥር አዲስ፣ ድረ ገፅ https://awashbank.com/
1.2. የአክሲዮን ማህበሩ የንግድ ምዝገባ ቁጥር KK/AA/2/0006147/2006፣
1.3. የአክሲዮን ማህበሩ የባንክ ስራ ፍቃድ ቁጥር LBB/001/94፣
1.4. የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) 41,241,008,000፣
1.5. የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) 20,611,000,000፣

## 2. የ28ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

1. ከህዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም. እስከ ህዳር 15 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ የተከናወኑትን የአዳዲስ አክሲዮኖች ግዥ፣ ዝውውር እና የባለአክሲዮኖችን ቁጥር /ብዛት/ ማሳወቅ፤
2. የዳይሬክተሮች ቦርድን እ.ኤ.አ. የ2022/23 ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥና መርምሮ ማፅደቅ፣
3. የውጭ ኦዲተሮችን እ.ኤ.አ. የ2022/23 ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዳመጥና መርምሮ ማፅደቅ፤
4. እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2023 ዓ.ም ስለተጠናቀቀው የሂሳብ ዓመት ትርፍ አደላደል የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ማፅደቅ፤
5. የዳይሬክተሮች ቦርድን እ.ኤ.አ የ2022/23 የሂሳብ ዓመት ክፍያ መወሰን፤
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ እ.ኤ.አ. የ2023/24 ወርሃዊ አበል ክፍያ መወሰን፣
7. የዕለቱን ጉባዔ ቃለ ጉባዔ ማጽደቅ፤

## 3. የ29ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

1. ከህዳር 16 ቀን 2016 ዓ.ም. እስከ ህዳር 14 ቀን 2017 ዓ.ም. ድረስ የተከናወኑትን የአዳዲስ አክሲዮኖች ግዥ፣ ዝውውር እና የባለአክሲዮኖችን ቁጥር /ብዛት/ ማሳወቅ፤
2. የዳይሬክተሮች ቦርድን እ.ኤ.አ. የ2023/24 ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥና መርምሮ ማፅደቅ፣
3. የውጭ ኦዲተሮችን እ.ኤ.አ. የ2023/24 ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዳመጥና መርምሮ ማፅደቅ፤
4. እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2024 ዓ.ም ስለተጠናቀቀው የሂሳብ ዓመት ትርፍ አደላደል የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ማፅደቅ፤
5. የዳይሬክተሮች ቦርድን እ.ኤ.አ የ2023/24 የሂሳብ ዓመት ክፍያ መወሰን፤
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ እ.ኤ.አ. የ2024/25 ወርሃዊ አበል ክፍያ መወሰን፣
7. የባንኩን የውጭ ኦዲተሮች መምረጥና ክፍያቸውን መወሰን፣
8. የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈፃፀም ፖሊሲ እና መመሪያ ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፤
9. የዕለቱን ጉባዔ ቃለ ጉባዔ ማጽደቅ፤

## 4. ማሳሰቢያ፡-

4.1. በጉባዔዎቹ ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ሥልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ከህዳር 9 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር 13 ቀን 2017 ዓ.ም 10፡00 ሰዓት ድረስ በባንኩ ዋና መ/ቤት ጀርባ በሚገኘው የባለአክሲዮኖች አገልግሎት ዋና ክፍል ቢሮ በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባዔው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን። ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ መሆኑን እናሳውቃለን።
4.2. የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባዔው ላይ መሳተፍ ይችላሉ። እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው እናሳውቃለን።
4.3. በተጨማሪም የድርጅት ተወካዮች የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ተመሳሳይ የሃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ወይም ድርጅቱን ወክለው እንዲገኙ የሚያረጋግጥ የተመዘገበ ቃለ ጉባኤ ወይም በውል አዋዋይ ፊት የተሰጠ የውክልና ሰነድ ይዘው መቅረብ ያለባቸው መሆኑን እናሳውቃለን።

የአዋሽ ባንክ አ.ማ

የዳይሬክተሮች ቦርድ